# ዘር እንደ ሙጀሌ

ከዮሐንስ ገዳ

እንዴት ይነቀላል፥
ጥፋቱ ምንድን ነው
በደሉስ ምንድን ነው
ዘር እንደንስሳ እንዴህ ሚታረደው

አዎ አማራ ነኝ
ዘሬ ካማራቸው
ኢትዮጵያዊነቴ ካንገሸገሻቸው
ካንገፈገፋቸው ካቅለሸለሻቸው
ችግሩ የነሱ ነው እኔ ምንላርጋቸው !

በገዛ ሀገሬ በአፅመ -ርስቴ
ለገዛ ሀገሬ በድንበር መዝሙቴ
ክብር እስትንፋሴን ለክብረት ሀገሬ
ሂጄ መገበሬ
ከድሉም በኋላ አንጀቴን በጠፍር
ወገቤን በድግ አስሬ ማረሴ
ምንድን ነው ጥፋቴ ምንድን ነው በደሌ
በሽታ ሆነ እንዴ ልክ እንደ ሙጀሌ
ካገር መባረሬ ከርስት መነቀሌ
እኮ ወዴት ሊሂድ አማራ በመሆኔ
ይህ ነወይ ወንጀሌ ?
እረ የእግዜር ያለህ ! እረ ያላህ ያለህ !
ጥፋቴን ሰላውቀው ሸንጎ ሳያቀርቡኝ
በዘሩ በሽታ ዘሬን አጠፉብኝ

ኤርትራ ተብሎ ከማጎል ሲባረር
መቼ ጮቤ ረግጥኩ ከበሮስ መች ደለቅሁ
ያለኝን ሰጥቼ ቀለብ ነው የሰፈርኩ
ስንቅ ነው ያስቋጠርኩ
እንባይን አፍስሼ
በለቅሶ ሸኝቼ
ነው የተለያየሁ
መቼ በሬን ዘጋሁ!
ይመጣሉ ብየ በተስፋ እየጓጓሁ

ጎዝቢ መረብ ምላሽ
ድቅ ባጎር ነጋሽ
ስጋብ መወዳታ
ናይ አህዋት ኢና
ስጋብ ፍፃሜ ዓለም
ተለያይተን አንቀርም

ብይ አለቀስኩ እንጅ

## መቼ ጠጣሁ ጠጅ

ዛሬ እኔ በፈንታዬ
በጥቃት ተራዬ
ያለ ግፍ በደሌ
ካገሬ ተነቀልኩ
በደሉ በዝቶብኝ የደም እምባ አለቀስኩ!

ደቡብ ሄጄ ብኖር
ሀገሬ ብየ ነው
ምሥራቅ ሄጄ ብኖር
ሀገሬ ብየ ነው
ምዕራብ ሄጄ ባርስ ማሳዬ ብየ ነው

አማራ ተብሎ ዘር እንዴት ይጠፋል?
ትውልድ ይመተራል?
ባድማስ ይፈልሳል?
ይኸማ ለታሪክ ለትውልድ ይከፋል
የኋላ የኋላ ምላሽ ይቸግራል
ማጣፊያው ይከብዳል !

ቻይናውም ዐረቡም
ሕንዱም ፓኪስታኑም
ያለ ሀገሩ መጥቶ ሀገሬን ወርሷታል
ደም በደም ታጅቦ ርስት ይመለሳል !
አንች ሀገረ- ኢትዮጵያ
የጀግኖች መብቀያ
ረባዳ መሬት
ታበቅይ እኮ ነበር ጀግና እንደ ደጋሴት
እንዴት ጀግና ጠፋ ዛሬ ከመቅፅበት !

እኔን ባሳገሩን ከሀገሬ ነቅሎ
ዘር-ማንዝሬን ጎልጉሎ- መንቅሎ
ዐባይ በረሃ ላይ ሬሳየን ጥሎ
መሳ ቤተሰቤን ዐባይ ወንዝ አራግፏል
ይንን የግፍ-ግፍ ያጤኗል ልብ ይሏል
የወገኖቸ ደም በከንቱን ይረሳል ?
በሰፈሩት ቁና መሰፈር ይቀራል ?

ከጉራ ፈርዳም ላይ
ልጆቸ እያዩ ልብሴን አስወልቆ
ርቃኔን ገርፏኛል
ይህን የግፍ ግፍ ታሪክ መዝግቦታል

ከደቡብ ሀገሬ÷
ከምሥራቅ መንደሬ
ከምዕራብ ደምበሬ
ከሰሜን ርስቴ
እያፈናቀለ በሬን ያጠረብኝ

የኢትዮጵያ ነቀርሳ ከወያኔ ሌላ ጠላትም የለብኝ !

ይህ የመለስ ራዕይ
የወያኔ ሳይንስ
የገማ ሀሳባቸው
እግር ያወጣና
ሀገሩን ደም በደም
ሲወራርስ በቃል
በማን ላይ ይከፋል
በማን ላይ ይብሳል ?

የነ ስብኀት ውሸት
ከእንትን የከረፋው
የነ አዜብ ስርቆት
ከእንትን የሚቀፈው
ግፉ ተንፈቅፍቆ
ጎተራው ሲሞላ
ልክ እንደ ሞጆሌ
የሚፈነቀለው
በአራቱ ማዕዘን
ቤቱን የተከለው
ሃሳዊ መሲሄው
ወያኔ ብቻ ነው

ቀኑም በርቶ አይቀር
ጨለማው ጨልሞ
ልክ እንደ ጉአሳ
አማራ ታልሞ
ሃያ አንድ ዓመታት
ቢጥሉት ከዋርካ ጋር አስረው
እሳት ቢለቁበትአመዱን ቢያወጡት
ጎጃሙን ከጎጃም ጨልፈው ሊያጠፉት
ዐባይ በረሃ ላይ ደሙን ካፈሰሱት
ከጉራ ፈርዳ ላይ ከርስቱ ነቅለውት
በሽፈራው ትዕዛዝ እንደ ከብት ከነዱት
አፈ-ሙዝ ወድረው ሳር ቅጥል ካስጋጡት
ሸዋ የከተመው ወራሪ ወያኔ
ባለ ፎቅ ታጁሩ
አዋሳ መሃሉ ኮብራ የሚነዳው
የሲዳሞን ቡና የሚሸመጥጠው
የጎጃሙን ማኛ የአሪሲውን ገብስ
የሚሸመጥጠው
በሰው ትካሻ ላይ የሚሽከረከረው
በትግራይ ስም ሽቃጭ
እፍኝ የማይሞላው ችጋራም ወያኔ
ከገዳም ያስወጣው ዋልድባን መነኩሴ
የኢትዮጵያ ሕዝብ ታግሎ ነፃነቱን ሲያገኝ
አስገጣይ ወያኔ እኔ አንተን አያረገኝ !

እኔ መች እንደ ደደቢቶች
ደደብ እሆናልሁ
ዘር በዘር ለማጥፋት
ለምን ማስናለሁ
ያለ አባቱ ክብሮ
አዲሳባን ወሮ
ፎቁን የተከለው
አሳሳና ገርባ
ሙስሊም የገደለው
መጅሊሱን አፍራሹ
ሲኖዶስ ከላሹ
ዋልድባን አርካሹ
ጋምቤላን ዘር አጥፊ
ጎንደርን የሸጠው
ለህንድ ለቻይናው
ለም መሬት ቸብቻቢው
በስንደቅ ዓላማው አምባሹ ለጣፊው
ዘሬን አጠፋ ብየ ዘሩን አላጠፋም
አጥፊው ወያኔ ነው ጠፊም ወያኔ  ነው
ከወያኔ ጠላት ኅብረቴን ፈጥሬ
እዳምጠዋለሁ ልክ እንደ ጥጥ ፍሬ
ይብላኝ ለወያኔ ድውይ ጊንጥ ብጤ
ዘር በዘር ሊያሰነሳ
ብዙሃን መሆኔ እረ እንዴት ተረሳ ?
አማራን በማጥፋት
ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት  ተነስቶ
ልክ እንደ ጌታው እንደ ግራዚያኒ
እንደ ጡት አባቱ እንደ ሙሶሊኒ
ጴጥሮስን ሊነቅል
ታሪክን ሊየጠፋ
የምኒልክን ሐውልት
በአፍ ጢሙ ሊደፋ
እርሱ ይጠፋል እንጅ  የታሪክ ገዳፋ

የሚንደፋደፈው ወያኔ ይጠፋል
በሕዝብ ነበልባል ነገ ይቃጠላል
በምደር-ኢትዮጵያ ዶግ አመድ ይሆናል
በከርሰ-መቃብሩ  አንድነት ይበስራል
ፍትኅ ርትዕ ነፃነት ይመጣል
የኢትዮጵያ ትንሣዔ ይነሳል ያፈራል
ይፈካል ያብባል፥  ያድግል  ስር ሰድዶ የፀናል!
ኢትዮጵያዊነትም ዘለዓለም ይኖራል !

ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃ ለዘለዓለም ትኖራለች !!!